# “ ሞት የሚፈራ ሙት”

EthioLion

*የጐንቻው!*

ከሰው ተራ ወርዶ ክብሩ ሲንኳሰስ፤
የሰብ ስብዕናው ቃል-አቡ ሲጣስ፤
ማተቡ ግማዱ ከአንገት ሲቦጠስ፤
የእምነቱ መሰረት ታቦቱ ሲረክስ፤
ስርዎ ስሪቱ ተክሉ ሰው ሲፈርስ፤
**የሞተው ሞት ፈርቶ ገዳዩን ሲያነግስ፤**
**ደመ ነፍስ ይኖራል የማይላወስ።**

በእራሱ መቃብር የሚንከላወስ፤
ሞት ኑሮ ሆነና የማይኰስኩስ፤
**ወዶ እሚጋቡበት የአደባብባይ ዳስ፤**
**ተዝካር መጠራሪያው የሰርጉ ድግስ፤**
በድን ያሸለበው ‘አስከሬኑ ነፍስ’፤
ሞትን ሙጥኝ ብሎ ኑሮ ዋቢ ቢስ፤
**በግፍ በበደሉ እንዳይከሰስ፤እንዳይወቀስ፤**
ዳኛና ህሊና ሙት እሚያስጨርስ፤
ሙቶ የሸፈተው ወንጀለኛ ነፍስ፤
**ቢጠሩት አይሰማ ቢወጉት ደንደስ።**

**ጥቃት፤ስቃይ፤ሊያመልጥ ማደንዘዣ ፈውስ፤**
የሞት ሞቱን ሙቶ፤ቁም እሚያስለቅስ፤
ኑሮን ሙቶ ሊሸሽ ምሽጉን ሲምስ፤
ትንሹን ሞት፤ሊሞት የሚልወሰወስ፤
ለቀን ጆሞራዎች እርካሽ በለስ፤
**ምናል? ፍራት ገድሎ፤ጀግና ቢወደስ።**

በአገር ባድባራችን ገዳማት፤ሲያፈርስ፤
የጻድቃኖች አጽም ቆፍሮ እሚምስ፤
‘ገነት ፍሬ’ አማሎ ‘ሸንኮራ እጽ-በለስ’፤
**ለእሸትም አይበቃ ለአውድማም አይደርስ፤**
ለአንዳችንም አይበጅ የባዕዳን ድግስ፤
‘ደም እየጠጁልን’ እንዳንጫረስ፤
**አያቀባብርም በግፍ ሞት ሲነግስ።**

ጥፋተኛው ልማት የሺህ ዘመንት ጦስ፤
ደን መንጥሮ ችግኝ ቀጠና ሊያውርስ፤
አረብ ጨው ያጋጠው ግራኙ **መለስ**፤
ቀኝ እጁ ‘**አላሙዲ**’ ‘የዮዲት’ ጥንስስ፤
የንጉሡ ጥዋ ሞልቶ አገር ሲፈስ፤
**አድባራት ሊያከትም ገዳማት ሊያፈርስ፤**
‘መስቀል የቆረጠ’ ‘ጨረቃው ንጉስ’፤
**መነኩሴ ሊያጠምቁ ‘ዋልድባ’ ድፍርስ፤**
ከቀያቴው አፈር ሥጋ ደም ልውስ፤
ሞትን ድል በሙቱ መነኰሳት ነፍስ፤
በአምላክ አገልጋዮች በንቁ መንፈስ፤
**ሞትን እንግደለው ምዕመናን ተነስ።**

*የጐንቻው!* yegonchaw@yahoo.co.uk

**Ethiopia Will Prevail!**

EthioLion.Com